ቁጥር፤ደ/መ/ቅ/ገ/ቤ/ክ/ኔ/ሪ/2/1998

ቀን፤ የካቲት 12 ቀን 1998 ዓ.ም
Date:- 19 February 2006

## <u>የሰበካ ኮሚቴ ምርጫ ሪፖርት፦</u>

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን !

በኔዘርላድ የ ኢ..ኦ.ተ.ቤ/ክ ውስጥ የመጀመሪያው ዙር ሰበካ ኮሚቴ ምርጫ ህዳር
1 ቀን 1995 ዓ.ም. በአምስተርዳም ፍኖተ ሰላም ሰንበት ት/ቤት ከመላው ኔዘርላንድ (በተለይ ከ3ቱ ትላልቅ ከተሞች) ከተውጣቱ እጩዎች መካከል ከምእመናን 6 አባላት ከዲያቆናት 2 አባላት በድምሩ 8 አባላት መመረጣቸው ይታወሳል። እነዚህ የተመረጡት 8 አባላት በዚያው ወር ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ሆላንድ ከመጡት ሊቀ ትጉሃን ቄስ ሙሉጌታ ስዩም ጋር በመሆን 9 አባላት ያለው ኮሚቴ በመመስረት ላለፉት 3 ዓመታት እግዚአብሔር በፈቀደው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ቆይቷል።

በዚህ በመጀመሪያው ዙር ከተመረጡት የሰበካ ኮሚቴ አባላት መካከል በድምሩ 3ቱ አባላት አገር መመልቀቅና በተለያዩ ምክንያቶች በኮሚቴው ውስጥ ስራ መስራት በማቆማቸው በምትካቸው ሌሎች አባላት ተመድበው ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

የቤተ ክርስቲያናችን ቃለ አዋዲ በሚያዘው መሰረት ይህ የሰበካ ኮሚቴ የ 3 አመት የግልጋሎቱ ጊዜ በማለፉ 2ኛ ዙር የሰበካ ኮሚቴ ምርጫ ለ12-02-2006 እንዲደረግ ኮሚቴው በወሰነው መሰረት በቅዳሴዎች፣ በኪዳን ጸሎት፣ በሰ/ት/ቤት ጉባዔዎች እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያናችን ድረ ገጽ ላይ በማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ከዚያም አስመራጭ ኮሚቴ ከሶስቱም ሰ/ት/ቤቶች ተመርጦ ለሰበካው ምርጫ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ከተደረጉ በኋላ ምርጫው በተያዘለት የቀጠሮ ቀን 12 Februari 2006 በሮተርዳም ከተማ በጽሃዬ ጽድቅ ሰ/ት/ቤት በተዘጋጀው የ 3ቱ ሰ/ት/ቤ/ት አጠቃላይ ጉባኤ ላይ የ2ኛው ዙር የሰበካው ኮሚቴ ምርጫ ተደረጓል።

የእለቱን መርሃ ግብር አባቶች ካህናትና ወንድሞች ዲያቆናት በጸሎት ከከፈቱ በኋላ ሰፊ የመዝሙር መርሃ ግብር ተከተለ። በመቀጠልም ሊቀ ትጉሃን ቄስ ሙሉጌታ ስዩም ስለ ቤተ ክርስቲያን ግልጋሎትና አንድ ምዕመን ለግልጋሎት እጩ ሲሆን ብሎም በኮሚቴ ውስጥ ገብቶ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ሲዘጋጅ እንደ ሃብት ሁል ጊዜ አብሮት ሊኖሩት ስለሚገቡ አራት አበይት ነጥቦች ላይ “… ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ…” የሐዋርያት ስራ 9፡6 በሚለው ርዕስ ሰፊ ትምህርት አስተምረዋል። እንዚህም አራት ነጥቦች ፤

1. ሁሉም በእግዚአብሄር ይቻላል ብሎ በሙሉ እምነት መቅረብ (መ/ነኽምያ 2፡20)
2. ሁል ጊዜ በንስሃ መመላለስ (ት/ኢሳይያስ 6፡ 5 - 8)
3. ትህትናን ልብስ ማድረግ (ኦሪት ዘጽዐት 3፡11) እና
4. በፍቅር መመላለስ (1ኛ ቆሮንጦስ 13፡13) ናቸው።



Adres:- EOTK in Nederland, D.M. Heilige Gabriel Kerk
Postbus 13001
2501 EA DEN HAAG
KvK Nr. 41160396
Postbank Gironummers:- 9520951 (Parochie=Sebeka) and 2958075 (Gebouwcomité)
Tel:- 070-3602267
06-26710596
06-26738079
www.Tewahedo.nl, info@tewahedo.nl

በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ሊገኝ የሚችለውን የእግዚአብሄርን ጸጋና ቸርነት ምን ያህል ብዙና የላቀ እንደሆነ ብናውቅ ኖሮ ሁላችንም ለማገልገል እንሽቀዳደም ነበረ ብለዋል።

በመቀጠልም የኮሚቴው የምርጫ ስነ ስርዓት በመቀጠል ከየከተማው 3 ምዕመናን ተመርጠው አልፈዋል። በዚህም መሰረት፦

<u>ከአምስተርዳምና አካባቢው</u>

1. አቶ ዳዊት ናቅአርጋቸው
2. ወ/ሮ ማሾ ፋንታዬ
3. አቶ ዘሪሁን ሽጉጤ

<u>ተጠባባቂዎች</u>

1. አቶ ስዩም ገ/እግዚአብሔር
2. ወ/ሮ የሺመቤት ከበደ

<u>ከዴንሃግና አካባቢው</u>

1. ወ/ሮ ፍቅርተ እሸቴ
2. ወ/ሮ አስራት ተክሌ
3. አቶ ታደሰ ጀራ

<u>ተጠባባቂዎች</u>

1. አቶ በፍቃዱ ካሳዬ
2. አቶ አማረ ይኩኑ

<u>ከሮተርዳም አካባቢው</u>

1. አቶ ታዬ ሁሴን
2. ወ/ሮ ገነት ሰብስቤ
3. ወ/ሮ ሃይማኖት ዘለቀ

<u>ተጠባባቂዎች</u>

1. አቶ ሽፈራው በላይነህ
2. አቶ ሙሉጌታ በቀለ

ከዲያቆናት ደግሞ ዲ/ን ዳንኤል ይፍሩ እና ዲ/ን ዮሴፍ አለማየሁ በካህንነታቸው በሰበካው ውስጥ ገብተው እንዲያገለግሉ ተወስኗል።

ከምርጫው በኋላም የመጀመሪያው ዙር የሰበካው ጸሐፊ ካለፈው ሪፖርት (18/04/2005) ወዲህ የተሰሩ ስራዎችንና የሂሳብ ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን በመቀጠልም በሪፖርቱ ላይ የጥያቄና መልስ ውይይት ተካሂዷል።

በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያናችን አስተዳዳሪ መላከ ሰላም አባ ተስፋ ማርያም ላቀ ለተመራጮች ምክርና ለአጠቃላይ ምእመን ቤተ ክርስቲያንን እንደራሳችን ቤት በማየት ቀርበን በተለያዩ የስራ ክፍሎች ገብተን እንድናገለግል በተለይም አሁን የተመረጡትን የኮሚቴ አባላት በስራቸው ሁሉ እንድናግዛቸው በመምከር ጉባኤውን ከሌሎች ካህናት ጋር በመሆን በጸሎት ዘግተዋል።

በሳምንቱ እሁድ 19 Feb. 2006 ካህናት አባቶች በሚመሩትና የ አስመራጭ ኮሚቴ ጸሀፊ እንደዚሁም የነባሩ የሰበካ ኮሚቴ ተወካዮች በተገኙበት አዲስ የተመረጠው ኮሚቴ በመጀመሪያው ስብሰባው ላይ የስራ ክፍፍል የተደረገ ሲሆን በዚህም መሰረት ከዚህ በታች ያለው ድልድል ተደርጓል።

የኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን በኔዘርላንድ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ በሁለተኛው ዙር የሰበካ ጉባኤ ምርጫ ላይ የተመረጡ ምዕመናንና የካህናት የስራ ምድብ።

**መላከ ሰላም አባ ተስፋ ማርያም ላቀ.......የሰበካው ዋና ሰብሳቢና የቤ/ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ**

1. ሊቀ ትጉሃን ሙሉጌታ ስዩም ...........የቤተ ክርስቲያን ህንጻ ኮሚቴ የበላይ ሀላፊ
2. አቶ ታዬ ሁሴን..............................ም/ሰብሳቢ
3. አቶ ዳዊት ናቅአርጋቸው..................ዋና ጸሐፊ እና የአምስተርዳም ሰ/ት/ቤት ተወካይ
4. ዲ/ን ዳንኤል ይፍሩ.........................ትምህርት ክፍል
5. ዲ/ን ዮሴፍ አለማየሁ.......................ትምህርት ክፍል
6. ወ/ሮ ገነት ሰብስቤ..........................ሂሳብ ክፍል
7. ወ/ሮ ማሾ ፋንታ ............................የህንጻ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ
8. ወ/ሮ ፍቅርተ እሸቴ.........................ገንዘብ ያዥ
9. አቶ ታደሰ ጀራ..............................የቁጥጥር ክፍል
10. ወ/ሮ አስራት ተክሌ........................የዴንሃግ ሰ/ት/ቤት ተወካይ
11. ወ/ሮ ሃይማኖት ዘለቀ......................የሮተርዳም ሰ/ት/ቤት ተወካይ
12. አቶ ዘሪሁን ሽንቁጤ........................ንብረት ክፍል

በመሆን ተመድበዋል።

ልዑል እግዚአብሔር አምላክ አገልግሎታችንን ይባርክልን

ሰበካ ጽ/ቤት
የካቲት 12 ቀን 1998 ዓ.ም.
(19 Februari 2006)
ዴን ሃግ